የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ – ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 14
ADDIS ABABA– 30th January, 2001


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፩/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
ለሴቶች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................................ ገፅ


## CONTENTS


Proclamation No. 231/2001
International Development Association Credit Agreement for financing the Women's Development Initiatives Project Ratification Proclamation ........................................ Page 146 2


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፩/፲፱፻፺፫

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሴቶች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር. ፫ ሚሊዮን ፰፻ሺህ (ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፳፰ ቀን ፪ሺ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሴቶች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፩/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፳፰ ቀን ፪ሺ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፬፻፯–ኢ.ቲ. የብድር ስምምነት ነው።

### PROCLAMATION NO. 231/2001

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 3,800,000 (three million eight hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Women's Development Initiatives Project, was signed in Washington D.C. on the 28th day of August, 2000;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 30th day of January, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Women's Development Initiatives Project Ratification Proclamation No. 231/2001.

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement No. 3407-ET signed in Washington D.C. on the 28th day of August, 2000, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፫ ሚሊዮን ፰፻ሺህ (ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 3,800,000 (three million eight hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 30th day of January, 2001.

Done at Addis Ababa, this 30th day of January, 2001.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE